ታሕሳስ 10 ቀን 2017 ዓም

ከኦሮሞ ሕዝብ ንቅናቄ ለኢትዮያ አድነት”ኦሕንኢአ”

## ክፍል አንድ

## ቀጥኜ ቢያየኝ ጅማት ለመነኝ!! ይላል ያገሬ ሰው፣

ሰሞኑን የሱዳን ወታደሮች የጎንደርን መሬት 40 ኪሎ ሜትር ወርረው መያዛቸውንና ሰብል ማቃጠላቸውን ከዚያም አልፈው በኢትዮጵያውያን አርሦ አደሮች ላይ እየተኮሱ መሆናቸውን በርካታ የዜና ማሰራጫዎች እየገለጹ ናቸው፥ ነገሩ አሳዛኝ ቢሆንም ሱዳን ሕሊውናችንን መፈታተን የጀመረችው ዛሬ ወይም ትላንት ሣይሆን ከዘመናት በፊት እንደሆነ ኢትዮጵያን በመከላከል ታሪካችን ውስጥ በብዙ ምዕራፎች ውስጥ ተጠቅሶ እናገኛለን፣

ሱዳን አገራችንን ከማጥቃት ተኘታ ወይም ጋብ ብላ እንደማትኖር የማያውቅ ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለንም፥ ከቅርብ ታሪካችን እንኳን ብንነሣ በአፄ ዮሃንስ ላይ የተጣለው አደጋ በሱዳን ደርቪሽ ሲሆን የንጉሣችን ደም እየቀረቀረን ሣለ ከእንግሊዝ ጋር በመተባበር መሬታችንን ወደ ራሷ ግዛት እንዲከለልላት አድርጋለች፥ በሱዳ አስተዳደር እንግሊዝ መድኔ ድረስ የነበረ ግዛታችንን ገምሶ ለሱዳኖች ቸረ፣ ይባስም ብሎ ሻለቃ ጐዌን የሚባል የእንግሊዝ የጦር ሠራዊት አባል የነበረ እስከ ጠገዴ ያለውን ለሱዳን ለመስጠት ካስማ ቸክሎላቸው ለሱዳኖች የመሟገቻ አጀንዳ ከፍቶላቸው ወደ አገሩ ተጓዘ፣ ብልጣብልጡ የሱዳን መንግሥት በውስጥ ችግራችን በተጣበብን ቁጥር ድንበራችንን እየገፋ ወገኖቻችንን እየገድለና እየዘረፈ ሰላማዊ ዜጎቻችንን እያደነ ይዟቸው ከራሱ ፍ/ቤት አቅርቦ እየፈረደባቸው እያንገላታቸው ነው፣ከዚያም ዘልቆ በዉስጥ ጉዳያችንም እጁን እየዶለ መክሰቡን ከማገኘ ወደ ጭልፋ እያሳደገው ነው፣ የነፃነት ትርጉም የማያዉቁት በጉርብትና መደጋገፍ የማይገባቸው ከሃዲ ሱዳኖችን እስከ መቸ እንታገሳቸው!! እስከ መቸስ ድረስ እየሞትን እንኑር!! ይህን ጥያቄ መመለስ የሚጋባው መላ ኢትዮጳዊ እንጂ የድንበር ኮሚቴ ብቻ አይደለም፣

በ19ነኛው ክፍለ ዘመን ማገባደጃ ላይ ጎንደር በደርቪሽ ሲቃጠል አፄ ዮሃንስ ሠራዊት መርተው የደርቪሽን የጀለቢያ ሠራዊት እስከ አምራኩባ አሳድደው እንደገረፏቸውና እርሳቸውም የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ለማስከበር ሲሉ መስዋዕት እንደከፈሉ ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሚያውቀው ሐቅ ነው፣ ሱዳን ለዘመናት በግብጽ ቅኝ ግዛት ሥር ስትማቅቅ ከዚያም አልፋ በእንግሊዝ ሥር ስትጨነቅ የደረሱላት ኢትዮጵያዉያን ብቻ ነበሩ፣ ለሱዳን ነጻነት ፈርመው ኃላፊነት የወሰዱ ኃይለ ሥላሴ ነበሩ፣ የሱዳንን ወታደር ለመጀመሪያ ጊዜ የደንብ ልብስ በገንዘባችን ገዝተው ያለበሷቸው ኃይለ ሥላሴ ነበሩ፣ በርካታ የጦር መኮንኖችን በዘመናዊ ወታደራዊ ሙያ ያሰለጠላቸው ኃይለ ሥላሴ ነበሩ፣ዘመናዊ የእንግዳ መቀበያ ሆተል የሠሩላቸው ኃይለ ሥላሴ ሲሆኑ የሆተሉ ስም ሣይቀየር ”ዛሬም የአፍሪካ ሆተል” በመባል ይጠራል፣ ከከሰላ እስከ ካርቱም ዘመናዊ የመኪና መንገድ የዘረጉላቸው ኃይለ ሥላሴ ነበሩ”

የኢትዮጵያ መንግስትና ሕዝብ ለሱዳን የዋለው በቀላሉ አይገመትም፥ ያበደ ውሻ አሳዳጊውን ይነክሳል" እንደተባለው ሱዳን ከኋላ ቀርነቷ ሣታገግም በኢትዮጵያ ላይ የጋረጠችው ሤራ ምንኛ አስከፊ እንደሆነ የምናየው ነው፤አፄ ኃይለ ሥላሴ የሱዳንን ሤራ በተጨባጭ ስለደረሱበት "ከኒሜሪ ወዳጅነት የዚያድ ባሬ ጠላትነት ይሻለኛል" ያሉት፤ ንጉሡ የሱዳንን ክህደት በማጠናቸው ካቢኔያቸው በሱዳን ሤራ ላይ ትኩረት እንዲሰጥ እንዳደረጉም ይሰማል፤ በእርግጥ ጦርነት እንዲታወጅባት አላሳሰቡም፥ ሱዳን ኢትዮጵያን የምታከብረው ብቅር ሣይሆን በጠብ ጊዜ እንደሆነ ሱዳን አገር ለረጅም ጊዜ የኖሩ ይናገራሉ፤

ለሱዳን በኢትዮጵያ አመራሮች የተዋለው በዚህ አጭር ጽሁፍ ተገልፆ የሚያልቅ ባይሆንም ሱዳኖች የፈፀሙብን በደል እጅግ በጣም ብዙ ናቸው፤ ዋናው ጥረታቸው አገራችንን ለአደጋ በማጋለጥ ሕዝባችንን እንዲበተን የማያደርጉት መሰሪ ሤራ የለም፤ በተለይ በስሜኑ የአገራችን ክፍል የሚነሱትን አገር አፍራሽ ወንበዴዎችን በመርዳት ወደር የሌለው ሤራ ፈጽማብናለች ኢትዮጵያ ለዛሬ ምስቅልቅልና አደጋ የደረሰችው በሱዳኖች ሤራ ነው፤ በተለይ ኢትዮጵያን ከቀይ ባሕር በር ለማግለል በዓረቦች የተነደፈውን መርሃ ግብር ለማስፈፀም ሱዳን ዋና ተባባሪና አስፈፃሚ ሆና ያላደረገችው ሤራ የለም፥ ተሳክቶላትም ኢትዮጵያን ሊያፈርሱ ከሚኳትኑት ጎን ተሰልፋ ኢትዮጵያ በውስጥ ችግራ ስትታመስ አጋጣሚው ተሳክቶላት ዛሬ የኢትዮጵያን መሬት ለመቀራመት እየበቃች ናት፥

ሱዳን የነፃነት ዳዴዋን ሣታጣጥም የኢትዮጵያን መሬት ለመውረር ከዚያም አልፋ ከቀይ ባሕር ልታቅበን አጀንዳ መሞነጫጨር ጀመረች፤ ሱዳን ራሷ የኖረ ታሪኳ እንደሚያመለክተው ከቀይ ባሕር የሚያገናኛት መስመር እንዳልነበራት ብዙ የታሪክ ማስረጃዎች አሉ፥ሰሞኑን ግብጽ ፖርት ሱዳን አጠገብ የሚገኘውን ሐላይብ የሚባል ወረዳ ከሱዳን ቀምታ ወደ ግዛቷ ስለቀላቀለች ግብጽ በዓለም ፍርድ ቤት ተከስሳ ስትጠየቅ ፥

"እርግጥ የሐላይብ ወረዳ የግብጽ አይደለም፥መሬቱ የኢትዮጵያ ነው፥ሱዳን የሚባል አገር በታሪክ የለም ፥ ኢትዮጵያ ደግሞ ወረዳውን አትጠቀምበትም፤ ስለዚህ በታሪክ የመኖሩ ጉዳይ ከጥያቄ የሌልች ሱዳን አገር አለኝ ብላ የመጠየቅ መብት የላትም፥ ሐላይብ የኢትዮጵያ መሬት ስለነበረ ኢትዮጵያ ዛሬም ሆነ ነገ ከጠየቀችን እንሰጣታለን"

ብላ የግብጽ መንግሥት መልስ ሲሰጥ ሱዳን "ይህም አለ ወይ" ብላ አፏን ይዛ ወደ ኋላ ብላለች፤ ክሱ ጉድ ያሰኛል የቀይ ባሕር ድርሻ የሌላት ሱዳን ጊዜ አደላትና፥" ኢትዮጵያ ከቀይ ባሕር ድርሻ የላትም ብላ ከአገር ሻጭ ከሀዲዎች በማበር ለመወሰን ችላለች፤ ነገሩ የምሳርና የመጥረቢያ ክስ ቢመስልም የሱዳን ሠራዊት ዛሬ አገራችንን ሊደፍር የቃጣው መንግሥት ተብየው ወያኔ ከጠላት በማበሩ ነው፥አዎን ጎን ሲሣሣ ጠላት ጥቃት ይበዛል ይባል የሌ !!

ሱዳን ፀረ ኢትዮጵያ የሚንቀሳቀሱትን አገር አፍራሾችን ስትረዳ የኖረች ብትሆንም ዛሬ ፀረ ወያኔና ፀረ ሻዐቢያ የሚንቀሳቀሱት ተቃዋሚዎችን በልዩ ዘዴ ከማዳከምም አልፋ ብዙ ተቃዋሚዎችን አሳልፋ ለኢትዮጵያ መንግሥት ሰጥታለች፤ ከተሰጡትም አብዛኛዎቹ በወያኔ እርምጃ ተወስዶባቸዋል፤ ተላልፈው ከተሰጡትም መካከል አንዳንዶቹ በቀጥታ በወያኔ ወታደሮች በምስጢር የተገደሉ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ታምመው ሕክምና እንዳያገኙ ተደርገው መስዋዕት ሆነዋል፥ ተላልፈው በሕክምና እጦት ሕይወታቸው ካለፈው መካከል ጀግናው

ቢትወደድ አጣናው ዋሴ አንዱ ነበሩ፣ ቢትወደድ አጣናው ዋሴ የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት መስራችና ም/ሊቀመንበር ነበሩ፣ ኢደኅ እንቅስቃሴ እንዳቆመ ትግሉን በአዲስ መልክ ለመጀመር የኢትዮጵያ አርበኞችም ግንባር ሲመሰረት ከመስራቾች አንዶ ነበሩ፥ በተለይ ተቃዋሚዎችን ወደ ትግሉ ወረዳ ለማስተላለፍ ብዙ ውጣዉረዶች ገጥሚቸዋል፣ በዚያ ሂደት ውስጥ የሱዳን ደህንነት በማያገባው ገብቶ በጣም አሰቃቂ እስር ቤት አስገብቷቸው ከፉኛ ተጉላልተዋል፣ከእርሳቸውም ጋር አስራ አምስት ሚልዮን የሱዳን ፓውንድ ወጭ አድርጋ ለአርበኞች የወታደር ልብስና ጫማ ገዝታ ለአርበኝ፤ች ለመላክ ስትል የተያዘችው ወ/ሮ አልማዝ ምትኩ ግፍ ተፈጽሞባታል፥ የአልማዝ ምትኩ የወታደር ልብስ መግዛቷ በሀቅ ላየ ሱዳንን የሚመልከት አልነበረም፥ የሱዳን ፀጥታዎች ግን ገንዘቧንም ዘርፈዋት ከዘጠኝ ወር በላይ ሰቆቃ ፈጽመውባታል፣ኢ ሰባአዊ ምርመራ ስለአካሄዱባት ለቀናት ራሷን ስታ ነበር፤

ቢትወደድ አጣናው ዋሴ የሱዳን ወታደር እጃቸውን ለመያዝ የቻለው በልዩ ዘዴ በማግባባት ነበር፣ እጃቸው የተያዘው እርሳቸው በጎንደርና በአከባቢው የሚንቀሳቀሰውን የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባሮችን ጎብብኝተው ሲመለሱ ነበር፣ሲያግባቧቸው..”ወያኔን ለመዋጋት መሣሪያ ሊሰጥዎት ነው” በሚል ማታለያ ቃል ነበር፣ ቢትወደድ የሱዳን መርማሪዎች በወንጀለኞች መዝገብ ቃላቸውን ሲቀበሏቸው ተላልፈው እንደሚሰጡ ተጠታጥረዋል፣ በተለይ ሰሜን ካርቱም ...”ደበቅ...” ከሚባል እሥር ቤት በነበሩ ጊዜ ወደ ቢሮ በተደጋጋሚ እየተጠሩ ይጠየቁ ነበር፣ ይጠየቁ የነበሩትም.... ደለሎ የሱዳን መሬት መሆኑን በፊርማቸው እንዲያረጋግጡ...ሲሆን ማረጋገጫውን ፊርማቸው ከሰጡ ግን ለወያኔ መንግሥት ተላልፈው እንደማይሰጡ ነበር ተስፋ ሲሰጧቸው የቆዩት፥ቢትወደድ ግን የሚሰጡዋቸው ምላሽ ... ” ደለሎ የልጄ የድግሴ የእርሻ ማሳ ነው፥ ድግሴ ያለ ምንም በደል በደርግ የተገደለ ሲሆን ተዝካሩን ሣላወጣ የልጄን ማሳ አሳልፌ የናንተ ነው ለማለት አልሞክርም፣ አሳልፋችሁ እንደምትሰጡኝ ቀደም ብዬ አውቀዋለሁ ፥ አሳልፋችሁ ብትሰጡኝ በአገሬ መሬት በተወለድኩበት ደብሬ አስከሬኔ ያርፋል.በአገሬ መሬት በወገኔ ታጅቤ ብቀበር ለልጆቼ ክብር ነው፥ ዛሬ በወያኔ አገዛዝ የልጄን ማሳ ልትወስዱ ትችሉ ይሆናል ፣ለኋላ ግን ተፀፃታችሁ የማትወጡት ዋጋ ትከፍላላችሁ፣ ይልቅስ በስሕተት በእጃችሁ የገባውን የገዳርፍን መሬት እንዳትጡ!! ”በማለት እቅጩን ነግረዋቸው ወደ እሥር ክፍላቸው ይመለሱ ነበር፣ መርማሪዎቹ ቢትወደድን ለማግባባት ቢሞክሩም ቃላቸው አልተለወጠም፣ በመጨረሻም እጅና እግራችው በብረት ሰንሰለት ታስሮ ከ 14 ተቃዋሚዎች ጋር ተላልፈው ለወያኔ ተሰጡ፣ እትዮጵያ እንደረሱ በማዕከላዊ እሥር ቤት ቆይታቸው ጊዜ በጠንካራ ሞራል አብረዋቸው የታሰሩትን ሲመክሯቸው የሱዳንን ዓላማ እንዲያመክኑ አደራ ይሉ ነበር፣ሞራላቸው እንደጥነከረ እሥራቸውን ቢገፉም አንድ ሐሙስ ቀን በቀላል ሕመም ተሰምቃቸው ወደ ክሊኒክ ተወስዱ፣ከጥቂት ቀናት በኋላ ከፉኛ መታመማቸው ተሰማ፣ ከአሥር ቀናት በኋል ማረፋችው ተነገረ ለሕልፈታቸው ምክንያት የሆነው ሕክምና እጦት መሆኑ ከሐኪሞች ዘንድ ተሰማ፥

ቢትወደድ አጣናው ዋሴ የዘር ወይም የጎሣ ልዩነት አይውቁም፣ ”ኢትዮጵያ አንድ ናት ” የሚለውን መሪህ በአጽኖት ያነሳሉ፣ የኦሮሞ ሕዝብ ንቅናቄ ለትዮጵያ [ኦሕንኢአ[ ለኢትዮጵያ

አንድነት ሲሉ የወደቁትን እንደነ ቢትወደድ አጠናው ዋሴ ያሉትን እንደሚያከብራቸው ሌሎችንም ለውደፊቱ በሰፊው ያነሳቸዋል፣

## <u>ክፍል ሁለት</u>

ሱዳን የኢትዮጵያን ግዛት ቆርሳ ለመውሰድ የቋመጠችው ዛሬ ሣይሆን ከነፃነቷ ማግስት ጀምራ እንደሆነ ማስረጃዎች ይጠቁማሉ፥ ከሁሉም በዓረቦች ተነድፎ የሱዳን አመራሮች ተግባራዊ ለማድረግ ላይ ታች የሚሉት <u>"የጠገዴ ኮሚቴ"</u> የሚለው ነው፥ ይህ ኮሚቴ የተመሠረተው ከሠላሳ አምስት ዓመት በፊት ሲሆን ዓላማው በነሐሴ 1875 ዓም ከዲቭ እሥማኤል ከወርኔር ሙንዝንጀር ጋር በተስማማው መሠረት ሲሆን ዉሉ "የከዲቭ እስማኤል ሠራዊት ወርሮ ከያዘው ከኢትዮጵያ ግዛት የአባይ ወንዝና ገባር ወንዞችና ዓባይ የሚሄዱባቸው ለግብጽ የሚሰጥ ሲሆን ሌላው በወረራ የሚያዘው ለሙንዚንጀር ይሆናል"የሚል ነበር፣ ያን ጊዜ ሱዳን የግብጽ ቅኝ ግዛት ነበረች፣ ያንን የግብጽን የቀን ሕልም ተግባራዊ ለማድረግ ሱዳን የጠገዴ ኮሚቴ አውቀረች፥

የጠገዴ ኮሚቴ የተመሠረተው በኦምዱሩማን ሲሆን አመራሮቹ የሱዳን ዶክቶሮችና የሱዳን ከፍተኛ ባለሥልጣኖች የዓረብ አማካሪዎች እንዳሉበትየነገራል፣ የኮሚተው እንቅስቃሴ እንዳይታውቅ አመራሩ ቢሮውን በየጊዜው ይቀያይራል፣ጽሕፈት ቤቱ በአሁኑ ጊዜ ጽ/ ቤቱ ሐጂ ዮሰፍ ካርቱም ሰሜን ምሥራቅ ይገኛል፣ አመራሩ የሚሰበሰበው በአሳቻ ሰዓት ሲሆን አከባቢው ለስለላ አይመችም፣

ለኢትዮጵያዊ ሁሉ ግልጽሊሆን የሚገባው ወደ ሱዳንና ግብጽ የሚሄዱ ሁለት ዓባዮች ናቸው፣ ሁለቱ ዓባዮች ከነገባሮቻቸው የማይዳስሱት የኢትዮጵያ መሬት የለም፣ስለሆነም የጠገዴ ኮሚቴ ፀረ ኢትዮጵያ መሆኑን ተግንዝበን አገራችንን ከሱዳንና ከዓረብ ሸረኞች የመጠበቅ ኃላፊነትና አደራ እንዳለብን መገዘብ ይኖርብናል፥

ሱዳን የጎረቤት ጠላቶች በተነሱብን ቁጥር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ እጇን ያላስገባችበት አጋጣሚ አልነበረም፥ ለወደፊቱም የሚቆጠቁጥ ምት ካልቀመሰች ዉዥንብር ከመፍጠር ትቆጠባለች ብሎ መጠበቅ የዋህነት ነው፣

ሱዳን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጥረት ነፃነቷን ከተቀዳጀችበት ቀን ጀምራ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያደረሰችው ግፍና በደል ተቆጥሮ ባያልቅም መጠቀስ ከሚገባቸው መካከል ከፊሎቹ 28 የስደተኛ መጠለያዎችን ከፍታ ከተመድ በቢሊዮን የሚገመት ዶላር ከዓለም ማህበረሰብ ስታጋብዝ ኖራለች፣ያን ጊዜ ነው አንድ የሱዳን ባለሥልጣን "በኢትዮጵያ ዉስጥ አንድ ቤት ሲፈርስ በሱዳን ዉስጥ ሦስት ቤት ይገነባል"ያለውን ሱዳን የረገጠ ኢትዮጵያዊ የሚያውቀው ሲሆን ቀጥተኛ ፊቸው በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚከሰተው ቀዉስ ለሱጋን ትርፍ ያስገኝላታል ለማለት ነው፣ ሦስቱ ሲጠቀሱ፥

የሚፈርው ከነጠቅላላ ንብረቱ ለሱዳን ይሸጣል

ለተፈናቃዩ ለሚሠራ መጠለያ ለሱዳን መንግሥት ግብር ይከፈላል

ተፈናቃዩ ለሱዳን አገልጋይ ሆኖ ጉልበቱ ይበዘብዛል

ሱዳን በኢትዮጵያውያን ላብና ደም ከሚታግበሰብሰው ገንዘብ ሌላ በኢትዮጵያ ላይ ስትፈርድ ኖራለች፣ ዛሬም ከሃዲ ወያኔን ተገን በማድረግ እየጨፈጨፈችን ነው፣ በ1969 ዓም ዕብርተኛው ዚያድ ባሬ መሬታችንን ሲወርር ሱዳን በምስጢር አንድ ተዋጊ ክፍለ ጦር ልካለት ብዙዎች መማረካቸውን ስትሰማ....አንድ ክፈለ ጦር የጠፋባት መሆኑን ለዓለም አሳወቀች፥የደርግ መንግሥትም ጦርነቱን በድል ስለደመደመ ለሱዳን ሤራ ትኩረት አልሰጠም፥ አባቶች ሲተርቱ "ባላጌን ቢንቁት የፈሩት ይመስላል" እንደተባለው ያን ጊዜ ደርግ ጨፍለቅ ቢያደርጋቸው ኖሮ ሕዝባችን ለዛሬ ዉርደት ባልበቃ ነበር፥ የሱዳን ገዢዎች በኢትዮጵያውያን ላይ ያደረሱት ግፍ ተቆጥሮ አያልቅም፥ በገዳርፍ ክልል ተዋዋ የሚባል በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ስደተኞች ከሃያ ዓመት በላይ የኖሩበትና የተመድ የዉሃ ቧንቧና ሌሎችን ያሟላውን መጠለያ የሱዳ መንግሥት በኃይል ሲያስለቅቅ ከአሥር ሺህ በላይ መቃብሮችን አፍርሶ የኢትዮጵያውያንን አጥንት አቃጥሏል፥አጥንቶቹ ለሦስት ወራት ጭሰዋል፥በተሰቡን ተዋዋ የቀበረ ኢትዮጵያዊ የሚያደርግ ጠፍቶት ወደ ጭሱ አከባቢ እየሄደ እንባውን ሲያያፈስ ነበር፣ በመጨረሻ የሱዳን መንግሥት በኢትዮጵያውያን መቃብር ላይ "የገዳርፍ ዩኒቨርሲቲ " ገንብቶ ዛሬ እያስተማረ ነው፥ ሱዳን የኢትዮጵያውያን በተክርስቲያን ለማራከስ ከነጫማችርው እየገቡ ይወጣሉ፥ ሱዳን ኢትዮጵያውያንን የምታንገላትውና ስበዕናቸውን የምትዳፈረው ከመንግስታችን ችላ ማለት ነው፥ ዛሬ በካርቱም ከተማ መኻል ሣጃና ከሚባል ቦታ በሁለተኛ የዓለም ጦርነት ጊዜ የተሰው እሥራኤላውያን በክብር ታጥሮ ይገኛል፣ በዝርዝሩ ውስጥ መግባት ባያፈልግም መቃብሩ ተክብሮ እንዲኖር የተደረገው በእሥራኤል መንግሥት ኃይል ነው፣

የኢትዮጵያ ሕዝብ ንቅናቄ ለኢትዮጵያ አንድነት[ኦሕን ኢአ' የሱዳንን ግፍና ንቀት በቀላሉ አይመለከትም፣ የወያኔ ትግሬ መንግሥት ለሱዳን የሰጠው ሰፊ መሬት የአማራ መሬት ብቻ ሳይሆን የኦሮሞ፣ የበኒሻንጉል፣የጋምቤላ፣የጉሙዝ ጭምር ሲሆን አማራው የድንበር ኮሚቴ አቋቁሞ ለብቻው የሞት ሽረት ትንቅንቅ ሲያደርግ ቆይቷል እያደረገም ነው፣የኦሕንኢአ የኮሚቴውን ቆራጥ አሠራር በአድናቆት እያነሳው ድንበሩን በማስመለሱ በኩል የሚመለከታቸው አካሎች ሁሉ በኮሚቴው እንዲካተቱ ጥሪ ያደርጋል፣ የኦሕንኢአ ከድንበር ኮሚቴው ጎን ለመቆም የሱዳንን ሤራ በማምከኑ ረገድም የሚጠበቅበትን ለመወጣት ዝግጁ መሆኑን ያረጋግጣል፣ አሁን በእንቅስቃሴ ላይ የሚገኘው የድንበር ኮሚቴም ሌሎችን ለማካተት በራቸውን ከፍተው እንዲቀበሉ ኦሕን ኢአ ያሳስባል፣ በተጨማሪ የጎንደር ጀግናው ሕዝባችን የሱዳንን እብርተኛ ሠራዊት አሳፍሮ ወደ መጣበት በማባረሩ የኦሕንኢአ ከፍተኛ ኩራት ተሰምቶታል፣

1... Dejene Jalata Geerarsa (Oromp3 )

2...Caala Daggafaa Sigisi Afuur Kuti New oromo 2017

3...Mix Tadassa Dhaii Bittan Buloomalle New Oromo Music

## አንድነታችን ለዘለዓለም ይኑር

## ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!